መልእክት ሰባት

## የመቅደሱ ዕቃዎች
## ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ 1 ነገ. 5፡15-18፤ 6፡7፣
9-10፣ 15-16፣ 23፣ 31-34፣ 36፤ 7፡14-15፣ 21

**I. ለእግዚአብሔር ግንባታ የሚሆኑ ዕቃዎች ለመሆን፣ ክርስቶስን በሞቱ (በጥድ እንደተመለከተው)፣ ክርስቶስን በትንሣኤው (በዝግባ እንደተመለከተው) እና ክርስቶስን እንደ መንፈስ (በወይራ እንጨት እንደተመለከተው) መለማመድ ያስፈልገናል፦**

ሀ. ሁሉን-ያካተተ የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ እና በሂደት ያለፈው የሦስታንዱ አምላክ መገኘት የሆነው የተሰቀለው እና ከሞት የተነሣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር መቅደስ፣ የክርስቶስ መተለቅ እና መስፋፋት የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ግንባታ ዕቃዎች እውነታ ነው—ፊልጵ. 1፡19-21፤ 1 ቆሮ. 3፡9፣ 12፣ 16-17።

ለ. እንደ የእግዚአብሔር መቅደስ ለቤተ ክርስቲያን መገንባት ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጸጋ (የሕይወት የበለጠገ አቅርቦት) ደጋግ መጋቢዎች ለመሆን እጅግ ሙሉ የሆነ የክርስቶስ ድሰታ ማግኘት እንችል ዘንድ የተሰቀለው እና ከሞት የተነሣው ክርስቶስ እንደ መንፈስ ራሱን ወደ ማንነታችን ውስጥ እንዲገነባ መፍቀድ ያስፈልገናል—ኤፌ. 3፡2፣ 16-17፤ 1 ጴጥ. 4፡10-11።

**II. ጥድ የተሰቀለውን ክርስቶስ ያመለክታል—1 ነገ. 6፡15፣ 34፤ ተዛ. ዘፍ. 6፡14፦**

ሀ. በጥንት ጊዜ አይሁዳውያን ከመቃብሮቻቸው በላይ የጥድ ዛፎችን ይተክሉ ነበር፤ ስለዚህ፣ ጥድ የክርስቶስን ስብዕና በሞቱ፣ የተሰቀለውን ክርስቶስ ያመለክታል—1 ቆሮ. 2፡2።

ለ. የመቅደሱ ደጆች የተሠሩት ከጥድ እንጨት ሲሆን የኪሩቤል እና የዘንባባ ዛፎች ምስል የተቀረጸባቸው ነበሩ—1 ነገ. 6፡34-35፤ ተዛ. ሕዝ. 41፡18-20፦

1. ኪሩቤል በፍጥረታት ላይ የተገለጠውን የጌታን ክብር ያመለክታሉ (10፡18፤ ዕብ. 9፡5)፣ የዘንባባ ዛፎች የክርስቶስን ድል እና ዘላለማዊውን እና ሁሌም የሚኖረውን የክርስቶስን ኃይል ያመለክታሉ (ሕዝ. 40፡16፤ ራእ. 7፡9)።
2. የዘንባባ ዛፎቹ እና ኪሩቤል በጥድ እንጨት ደጆቹ ላይ መቀረጻቸው የክርስቶስ ድል እና የጌታ ክብር በመከራዎች በኩል ወደ ማንነታችን ውስጥ "እንደተረቀጹ" ያመለክታል—ሐዋ. 16፡7፤ ፊልጵ. 3፡10፤ 2 ቆሮ. 4፡10-12።

**III. ዝግባ ከሞት የተነሣውን ክርስቶስ ያመለክታል—1 ነገ. 6፡9-10፣ 15-16፣ 36፦**

ሀ. የዝግባ ዛፍ በሊባኖስ ተራሮች ላይ ያድጋል፤ ስለዚህ፣ ዝግባ በትንሣኤ ያለውን የክርስቶስን ስብዕና፣ ከሞት የተነሣውን ክርስቶስ ያመለክታል—መዝ. 104፡16፤ መኃ. 4፡8።

ለ. ከሞት የተነሣው እና የዐረገው ክርስቶስ እንደ ንጉሥ ከዳዊት ቤት የሆነ ግርማዊ እና ድንቅ ዝግባ ነው—ሕዝ. 17፡22-23፤ ሮሜ 1፡3-4፤ ሐዋ. 2፡22-24፣ 32-36፤ ዕብ. 2፡9።

ሐ. በደስታና በልምላሜ ተሞልተን በሽምግልና ፍሬያችንን ባለማቋረጥ በመስጠት በአምላካችን አደባባይ ውስጥ ስናብብ በያሕዌ ቤት ውስጥ ተተክለን በሕይወት እናድግ ዘንድ እንደ ሊባኖስ ዛፎች ሥሮቻችንን ወደ ክርስቶስ ውስጥ የምንሰድድ ልንሆን ያስፈልገናል—ሆሴ. 14፡5-9፤ መዝ. 92፡12-14፤ 2 ነገ. 19፡30።

መ. ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ የትንሣኤ ኃይል መያዣ እና ኀተራ ናት፤ ይህ ኃይል በክርስቶስ ውስጥ በሠራ ጊዜ፣ ራስ እንዲሆን አደረገው፤ ይህ ኃይል በእኛ ውስጥ ሲሠራ፣ አካሉ ያደርገናል—ኤፌ. 1፡19-23፤ ሮሜ 8፡2፣ 11፤ 12፡1-2፤ ፊልጵ. 3፡10።

**IV. የወይራ እንጨት የተለወጠውን ክርስቶስ ሕይወት እንደሚሰጠው መንፈስ ያመለክታል—1 ነገ. 6፡23፣ 31-33፤ 1 ቆሮ. 15፡45፦**

ሀ. የወይራ ዘይት የእግዚአብሔርን መንፈስ በምሳሌ ያሳያል፤ ስለዚህ፣ የወይራ እንጨት በእግዚአብሔር መንፈስ ውስጥ ያለውን የክርስቶስን ስብዕና፣ እንደ ቅባቱ የተቀመመው መንፈስ ጭምር የሆነውን የተቀባውን ክርስቶስ ያመለክታል—ዕብ. 1፡9፤ 2 ቆሮ. 1፡21፤ 1 ዮሐ. 2፡20፣ 27፤ ዘጸ. 30፡25፣ 30።

ለ. ክርስቶስን ለመደሰት እንደ ለመለመው የወይራ ዛፍ በእርሱ ላይ በተጋቦ የተገጠምን የክርስቶስ ቅርንጫፎች ነን (ሮሜ 11፡17፣ 24)፤ ሕይወት-የሚሰጠው መንፈስ እንደ ሰማያዊው የወይራ ዛፍ የክርስቶስ ሕይወት-ጭማቂ ነው፤ እንደ

ሰማያዊው የወይራ ዛፍ ስብ፣ ጭማቂ፣ የክርስቶስን ብልጥግናዎች ለመካፈል ከፈለግን፣ ሕይወት-የሚሰጠውን መንፈስ እንደ የክርስቶስን ሕይወት-ጭማቂ መንካት ያስፈልገናል (ሉቃ. 23፡31፤ ተዛ. መዝ. 92፡13-14፤ 36፡8-9)፦

1. ከክርስቶስ ጋር በተጋቦ መጋጠማችን የተከናወነው በመንፈሳችን ስለሆነ፣ መንፈሳችንን ያለማቋረጥ ማንቀሳቀስ ያስፈልገናል፤ "ኦ ጌታ፣ ኦ ጌታ" ብለን ጌታን ስንጠራው፣ መንፈሳችንን እናንቀሳቅሳለን፣ ጌታንም ሕይወት-እንደሚሰጠው መንፈስ ወዲያውኑ እንካፈለዋለን—ሮሜ 8፡16፤ 1 ቆሮ. 6፡17፤ ሮሜ 10፡9-13።
2. የክርስቶስን ብልጥግናዎች የምንደሰትበት ሌላው መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ እና ለእያንዳንዱ ቃል አሜን ማለት ነው፤ በዚህ መንፈሳችንን እናንቀሳቅሳለን፣ ጌታን እንነካዋለን፣ እንደሰተዋለን እና ሁሉን-ያካተተውን መንፈስ እንደ ስብ እንካፈላለን—መዝ. 106፡48፤ ነህ. 8፡6፤ 2 ቆሮ. 1፡20፤ ራእ. 19፡4፤ ኤፌ. 6፡17-18።

ሐ. "ከተፈጥሮ በተቃራኒ" ወደ ክርስቶስ ውስጥ በተጋቦ እንደተገጠምን ማየት ያስፈልገናል፤ *ከተፈጥሮ በተቃራኒ* ማለት "ከእኔነት በተቃራኒ" ማለት ነው—ሮሜ 11፡24፦

1. ከአሮጌው ሰዋችን የሆነ ነገር ሁሉ የጌታን ባሕርይ ይቃረናል፤ የእኛ ባሕርይ ኃጢአተኛው ባሕርይ ነው፣ የጌታ ባሕርይ መለኮታዊው፣ መንፈሳዊው እና ቅዱሱ ባሕርይ ነው—ገላ. 5፡16-17፤ 2 ጴጥ. 1፡4።
2. ክርስቶስን ከብልጥግናዎቹ ጋር እንደ የወይራው ዛፍ ለመካፈል፣ እንደ የበረሃ ቅርንጫፎች ከአሮጌ መነሻችን፣ ከአሮጌ ታሪካችን፣ ከአሮጌ ሕይወታችን፣ ከአሮጌ ልማዶቻችን እና ከአሮጌ ወጋችን ሙሉ በሙሉ መቆረጥ አለብን—ሮሜ 11፡24፤ ተዛ. ኤፌ. 4፡22-24።
3. ከአሮጌ የአኗኗር ዘይቤአችን መቆረጥን ለመለማመድ እና ወደ ክርስቶስ ውስጥ በተጋቦ የመጋጠምን ልምምድ ለመደሰት፣ ስሙን ለመጥራት እና ቃሉን እየጸለዩ-ለማንበብ መንፈሳችንን ማንቀሳቀስ ያስፈልገናል—ሮሜ 10፡6-8፤ ኤፌ. 6፡17-18።

መ. ሮሜ 11 እንደ የወይራ ዛፍ "ወይራዎችን" ለማፍራት እና መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክተውን የሚያጽናና ዘይት ለመስጠት የክርስቶስ ቅርንጫፎች እንደሆንን ይገልጣል፤ ዮሐንስ 15 እንደ የወይኑ ተክል "ወይኖችን" ለማፍራት እና መለኮታዊውን ሕይወት የሚያመለክተውን የሚያነቃቃ የወይን ጠጅ ለመስጠት የክርስቶስ ቅርንጫፎች እንደሆንን ይገልጣል (ቁ. 5)፤ በሉቃስ 10 ደጉ ሳምራዊ ሊሞት ባለው ሰው ቁስሎች ላይ ዘይት እና የወይን ጠጅ አፍስሷል (ቁ. 33-34)፦

1. ዘይት እና የወይን ጠጅ በአንድ ላይ ለሰዎች ፈውስ ይሆናሉ፤ ይበልጥ ስሙን በመጥራት እና ቃሉን እየጸለይን-በማንበብ በጌታ ስንኖር፣ ውስጣቸው በስነልቦና ወደ ቆሰሉና ተስፋ ወደ ቆረጡ ሰዎች ውስጥ የምናፈስሰው ዘይት እና የወይን ጠጅ ለመስጠት ይበልጥ "ወይራዎች" እና "ወይኖች" እናፈራለን።
2. የወይራ ዛፍ ዘይት እግዚአብሔርን እና ሰውን ለማክበር ጥቅም ላይ ይውል ነበር (መሳ. 9፡8-9)፣ ይህም በመንፈስ የሚመላለሱ እግዚአብሔርን እንደሚያከብሩ (ገላ. 5፡16፣ 25) እና መንፈስን [ለሰው] የሚያገለግሉ ሰውን እንደሚያከብሩ (2 ቆሮ. 3፡6፣ 8፤ ፊልጵ. 3፡3) ያመለክታል።
3. የወይን ተክል የወይን ጠጅ እግዚአብሔርን እና ሰውን ደስ ለማሰኘት ጥቅም ላይ ይውል ነበር (መሳ. 9፡12-13)፣ ይህም ክርስቶስን እንደ የመሥዋዕትነት እና የሚያነቃቃ ሕይወታቸው የሚደሰቱ እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኙ (ማቴ. 9፡17) እና እንደ የመሥዋዕትነት እና የሚያነቃቃ ሕይወታቸው ክርስቶስን [ለሰው] የሚያገለግሉ ሰውን ደስ እንደሚያሰኙ (2 ቆሮ. 3፡6፤ ፊልጵ. 2፡17፤ 2 ጢሞ. 4፡6) ያመለክታል።

## V. የመቅደሱ አዕማድ የእግዚአብሔርን ፍርድ በማመልከት የተሠሩት ከናስ ነበር—1 ነገ. 7፡14-15፣ 21፤ ራእ. 3፡12፤ 21፡22፦

ሀ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዓምድ የአካሉን ሕይወት በተግባር በመለማመድ ውስጥ በመለወጥ በኩል የሆነው የእግዚአብሔር ግንባታ ምልክት፣ ምስክር ነው—ዘፍ. 28፡22፤ 1 ነገ. 7፡15-22፤ ገላ. 2፡9፤ 1 ጢሞ. 3፡15፤ ራእ. 3፡12፤ ሮሜ 12፡2፤ ኤፌ. 4፡11-12።

ለ. ለእግዚአብሔር ጠቃሚ የሆኑ ሰዎች በሥጋ የሆኑ፣ ለመሞት እና ለመቀበር እንጂ ለምንም የማይገቡ ሰዎች እንደሆኑ በመገንዘብ ያለማቋረጥ በእግዚአብሔር ፍርድ (ናስ) ሥር ናቸው—መዝ. 51፡5፤ ዘጸ. 4፡1-9፤ ሮሜ 7፡18፤ ማቴ. 3፡16-17፦

1. በአማኞች መካከል ላለው መከፋፈል እና ፍሬ አልባነት ለሁለቱም ምክንያቱ ምንም ናስ፣ ምንም የእግዚአብሔር ፍርድ አለመኖሩ ነው፤ በምትኩ ትዕቢት፣ በራስ-መመካት፣ ከወቀሳ ሆነ ከጥርጣሬ ራስን-ነጻ ማውጣት፣ ራስን ማጽደቅ፣ ራስን ተቀባይ ማድረግ፣ ለራስ-መሚገት፣ የራስ-ጽድቅ እና ሌሎችን በእረኝነት በመንከባከብ እና በመፈለግ ፈንታ መኮነን እና መቆጣጠር አለ—16፡24፤ ሉቃ. 9፡54-55።

2. ጌታን ስንወደው እና እንደ የናሱ ሰው ስንለማመደው (ሕዝ. 40፡3)፣ እርሱ ልዩ ፍቅራችን፣ ወሰን የሌለው ገርነታችን፣ አቻ የሌለው ታማኝነታችን፣ ፍጹም ትሕትናችን፣ ፍጹም ንጽሕናችን፣ እጅግ ከፍተኛው ቅድስናችን እና ጽድቃችን፣ እና ብሩህነታችንና ቅንነታችን ይሆናል (ፊልጵ. 4፡5-8)።

ሐ. በመቅደሱ ውስጥ በነበሩት አዕማድ ራስ ላይ "በአዕማዱም ራስ ላይ የነበሩትን ጕልላቶች ይሸፍኑ ዘንድ ሁለት እንደ መርበብ *ሥራ* [ከሰንሰለት *ሥራ ጋር*] አደረገ"፤ ይህ የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ግንባታ ውስጥ ያሉት እነዚህ አዕማድ የሚኖሩበትን እና የተወሳሰበ ኃላፊነት የሚሸከሙበትን የተወሳሰበ እና የተደበላለቀ ሁኔታ ያመለክታል (1 ነገ 7፡17፤ 2 ቆሮ. 1፡12፤ 4፡7-8)፤ በጕልላቶቹ ጫፍ ላይ የሱፍ አበባዎች እና ሮማኖች ነበሩ (1 ነገ. 7፡18-20)፡-

1. የሱፍ አበባዎች በእግዚአብሔር የማመን ሕይወትን፣ እኛ በሆንነው ሳይሆን እግዚአብሔር ለእኛ በሆነው ነገር የመኖር ሕይወትን ያመለክታሉ፤ ናሱ ማለት "እኔ አይደለሁም" ማለት ሲሆን የሱፍ አበባ ማለት "ነገር ግን ክርስቶስ" ማለት ነው—*መኃ*. 2፡1-2፤ ማቴ. 6፡28፣ 30፤ 2 ቆሮ. 5፡4፤ ገላ. 2፡20።
2. በጕልላቶቹ ጌጦች ላይ ያሉት ሮማኖች እንደ ሕይወት የክርስቶስን ብልጥግናዎች ሙላት፣ ብዛት እና ውበት እንዲሁም መገለጥ ያመለክታሉ—ፊልጵ. 1፡19-21፤ ኤፌ. 1፡22-23፤ 3፡19።
3. በመርበብ *ሥራ*ው መስቀል እና በሰንሰለት *ሥራ*ው መገደብ በሕይወት ለሆነው ለእግዚአብሔር ግንባታ የመለኮታዊውን ሕይወት ብልጥግናዎች ለመግለጥ በእግዚአብሔር የማመንን ንጹሕ፣ ቀላል ሕይወት መኖር እንችላለን።

**VI. የመቅደሱ ድንጋዮች በልውጠት የክርስቶስን ስብዕና ፣ የተለወጠውን ክርስቶስ ያመለክታሉ—1 ነገ. 5፡15-18፤ 6፡7፣ 36፤ 1 ዜና 29፡2፤ 2 ዜና 3፡6፡-**

ሀ. እንደ አምላክ፣ ክርስቶስ በተሠግዎው የሰውን *ሥጋ* ለበሰ፤ በ*ሥጋ* ያለ ሰው፣ በአሮጌው ፍጥረት ውስጥ ያለ ሰው ከሆነ በኋላ፣ በስብዕና ክፍሉ መለወጥ ያስፈልገው ነበር—ሮሜ 1፡3-4።

ለ. እንዲህ ያለው የተለወጠው ክርስቶስ አሁን የእግዚአብሔር ግንባታ ሕያዉ ድንጋይ፣ የመሠረቱ ድንጋይ፣ የማዕዘኑ ድንጋይ እና የመደምደሚያው ድንጋይ ነው—1 ጴጥ. 2፡4፤ ኢሳ. 28፡16፤ 1 ቆሮ. 3፡11፤ ኤፌ. 2፡20፤ 1 ጴጥ. 2፡6፤ ዘካ. 4፡7፤ 3፡9፤ ራእ. 5፡6፤ 4፡3፤ 21፡11።

ሐ. በተጨማሪም በመቅደሱ ውስጥ ያሉት ድንጋዮች ድንጋይ በሆነው በክርስቶስ የተለወጡትን በክርስቶስ የሚያምኑ አማኞችን ያመለክታሉ—ማቴ. 16፡18፤ ዮሐ. 1፡42፤ 1 ጴጥ. 2፡4-7፤ ራእ. 21፡11፣ 14፣ 18-21፤ ተዛ. ዳን. 2፡34-35፣ 44-45።

መ. አዲስ ኪዳን ስለ ሕያዋን ድንጋዮች ይናገራል (1 ጴጥ. 2፡5)፣ ብሉይ ኪዳን ስለ ተጠረቡ ድንጋዮች ይናገራል (1 ነገ. 5፡15፣ 17-18፤ 6፡7)፤ ለቤተ ክርስቲያን ግንባታ ጥቅም ላይ የሚውሉት ድንጋዮች ውስጣዊ በሆነ መልኩ ሕያዋን እና ውጫዊ በሆነ መልኩ የተጠረቡ (የታደቡ) መሆን አለባቸው (2 ቆሮ. 4፡16)፡-

1. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳንድ ወንድሞች እና እኅቶች ከካባ አሁን ከተፈለጡ፣ ስል ጠርዞች ካሏቸው "ካልተገሩ" ድንጋዮች ጋር መነጻጸር ይችላሉ፤ ሲነኩ፣ ሰዎች እንዲጎዱ እና የማይመች ስሜት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ።
2. በላያቸው ለመገንባት፣ ከሌሎች ጋር ለመቀናጀት እና ለማገልገል፣ ከሌሎች ጋር ውጊያውን ለመዋጋት ወይም ታቦቱን ከሌሎች ጋር ለመሸከም በበቂ መልኩ ጽኑ አይደሉም።

**VII. ለቤተ ክርስቲያን እንደ የእግዚአብሔር መቅደስ መገንባት ዕለት ዕለት ለመታደስ እና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለእግዚአብሔር ክብር፣ ከክብር ወደ ክብር ለመለወጥ በትንሣኤው ኃይል ሞቱን እንመስል ዘንድ፣ እውነተኛው የክርስቲያን ሕይወት የተሰቀለው እና ከሞት የተነሣው ክርስቶስ ሕይወት እንደሚሰጠው መንፈስ ወደ ማንነታችን ውስጥ እየተገነባ ያለበት ሕይወት ነው—ፊልጵ. 3፡10፤ 2 ቆሮ. 3፡18፤ 4፡16-18፤ ኤፌ. 3፡21።**

*© 2022 Living Stream Ministry*